የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 50
ADDIS ABABA 19th April, 2019

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፮/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.................ገጽ ፲፩ሺ፪፻፮

**Content**

proclamation No. 1136/2019

International Development Association Loan Agreement for financing Resilient Landscapes and Livelihoods Project Ratification Proclamation ……………………………………………Page 11206

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፮/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፸ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ ሚልዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ኅዳር ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

PROCLAMATION No. 1136/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHERE AS,** the Loan Agreement, between the Federal Democratic Depublic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 70,600,000 SDR (seventy million six hundred thousand SDR) Special Drawing Rights for financing resilient landscapes and livelihoods project, was signed in Addis Ababa on 7th day of December 2018;

**WHERE AS,** the House of People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of April, 2019.

**NOW, THERFORE**, in accordance with article 55 sub-articles (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፮ /፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ኅዳር ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6312-ET ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ ሚልዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Resilient Landscapes and Livelihoods Project Ratification Proclamation No. 1136/2019".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 6312-ET signed in addis ababa on 7th day of december 2018 between the federal democratic republic of ethiopia and the international development association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The ministry of finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of equivalent to 70,600,000 SDR (seventy million six hundred thousand SDR) special drawing rights in accordance with the terms and conditions set forth in the loan agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

Done at Addis Ababa, this 19th day of April,2019.

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**